ሐዋርያ
ሚያዚያ 1999 ዓ.ም

## ርዕሰ አንቀፅ

# አማራጭ የሌለው ምርጫ

ለሁሉም ወገን ሊበጁና ውጤታቸውም አመርቂ ሊሆኑ የሚችሉ የፖለቲካ አማራጮች፥ ዛሬም እንደትላንቱ በሥልጣኑ ማማ ላይ በተቀመጠው አምባገነናዊ መንግሥት ተቀባይነት አለማግኘት እጣ ፋንታቸው ሆኖ፥ ለተራዘመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ መደላድል ሆነዋል፡፡ እንዲህም ሆነና እነሆ፥ ከ1960ዎቹ ዓመታት መግቢያ ዋዜማ ጀምሮ መነሰም የጀመረው የመሠረታዊ ለውጥ ጥሪ አታሞ፥ ብዙዎቹን በቃናው ለዘመናት መስጦ፥ ጥቂቶቹን ደግሞ በየደረጃው አስክሮ በማደናበር፥ በሕዝብ ስሜት ላይ ዳንኪራ እያስረገጠ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህ ላለፉት 40 ዓመታት ያህል በለውጥ ሐዋርያቱና ደቀመዛሙርቱ ትክሻ ላይ ተነግቶ፥ ያለማቋረጥ የሚተመው ድምጸ-ምልአት፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ናር ጎላ እያለ በመቀጠሉ፥ እፁብ ድንቅ ዜማው የስሜት ህዋሳትን እየነዘረ፥ ሕዝበ-አዳሙን ከተቀመጠበት እየወዘወዘ ነው፡፡ ስለሆነም፥ ሰማይና መሬት ተለያይተው ወደ ነገው ብርሃን ከመሸጋገራችን በፊት፥ የአደራሹ ሕዝብ ወግ ባህል ነውና ጨፍሮ መርቆ ለመሰነባበት፥ መድረኩ ላይ ወጥቶ ማረግረግ ይጠበቅበታል፡፡

በተራዘመውና የኢትዮጵያን ሕዝብ እዳ በቁና በሰፈረው የትግል ዐውደ ሂደት ውስጥ፥ በፖለቲካው ላዕላይ ላይ፥ ምን ወድቆ ምን ተነሳ፥ የሀገሪቱ ምጣኔ ሃብትና የሕዝቡ "የዕለት ጉርስ የቀን ልብስ" ደረጃስ የት ላይ ነው፥ የሚሉትን አይስቱዋቸው ጥያቄዎችና፥ እድንዲሁም በሀገሪቱና በሕዝቧ ላይ የደረሰውን ህልቆ መሳፍርት የለሽ ውጣ ውረድ ሳንዘነጋ፥ በዚህ እልህ አስጨራሽ የተራዘመ የትግል ጎዞ ላይ፥ ብዙ የማያዳግሙ ድሎች መገኘታቸው ግን ከቶውኑ ሊዘነጉ አይገባም፡፡ ሕዝቡ የገበየው ዕውቀት ለመብቱ ተደራጅቶ ጨቋኝ ገዥዎችን መጎርበጥ ብቻ ሳይሆን፥ በአመፃው ነበልባል እየገረፈ መቅጣትን፥ በጠንካራ ክንዱ ሰባብሮ የዶግ አመድ ማድረግንም አውቆበታል፡፡ ከንጉሡ ፍጹማዊ ሁዋላ ቀር ሥርዓት ተመንጥቆ መውጣት የተቻለው፥ በራሱ በሕዝብ ትግልና አመጽ ነው፡፡ "ትሻልን ሰድጀ ትብስን አመጣሁ" ባዩን ናፋቂ ዘፈን፥ ማንጎራጎር ለሚፈልጉት ትተን፥ ሕዝቡ ግን ቢያንስ ግፈኞችን የመቃወም መብቱንና፥ በትግል አመጽ ነጻ የመውጣት ችሎታውን አስመስክሮበት አልፏል፡፡ የ"መሬት ላራሹ" ጥያቄ ትክክለኛ ግቡን ስቶ ከግለሰብ የመሬት ከበርቴዎች እጅ ወደ ተከታታይ አምባገነናዊ መንግሥታት ጉያ ቢወድቅም፥ ሥሪቱን ደምስሶ ኢትዮጵያ የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንጅ የጥቂት ሞልቃቆች ብቻ እንዳልልሆነች የሚያረጋግጠውን የግንዛቤ ድል ተጎናጽፎበታል፡፡ ጠቆር ቀላ፥ ከርደድ ለስለስ ያሉ ዜጎች፥ በኢትዮጵያዊነታቸው ሁሉም እኩልና ብርቅ መሆናቸውን፥ ጥያቄ በማያስነሳ ሁኔታ አስመዝግቦ አልፏል፡፡

በደም እጆቹን ታጥቦ በንጹህ ደም የተለቃለቀው ወታደራዊ ሥርዓት፥ በታሪካችን ምዕራፍ ላይ የእልቂት ታሪክ ክታቡን ወርውሮ የጠፋው፥ ዳር እስከ ዳር በተቀጣጠለ ሕዝባዊ ትግል ተዋክቦ ነው፡፡ ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉቱ ጠባብ ትምክህተኞች፥ "እኛ አሸነፍነው" እያሉ እንደሚገሰሉት ሳይሆን፥ ያ አረመኔ መንግሥት በሕዝብ ትግል መንምኖ ነበር የተበጠሰው፡፡ የወያኔ/ኢህአዴግ "እኔ ወንዱ!" የፉከራ ዝላይ፥ ቁመቱ እዚያው ላይ ነውና ብዙም ርዝመት የለውም፡፡ በወታደራዊው መንግሥትና በሕዝብ መካከል በተደረገው ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ የትግል ፍልሚያ፥ ሕዝቡና ታጋይ ለውጥ ፈላጊ ሃይሎች በአረምኔያዊው ጭፍጨፋ ተዳክመው በነበሩበት፥ የጠላትም ሃይል ዝሎ በተንገዳገደበት አጋጣሚ፥ የዛሬዎቹ "ማን ችሎን" ባዮች በአዲስ ጉልበትና በባእዳን ታጅበው ተንደርድረው በመግባት፥ ደርግን አሸነፍን ሲሉ የታሪክ ዝርፊያ ጀመሩ፡፡ የዚህ አይነቱ ቅጥፈታቸው ተጨማሪ የሚሆነው ደግሞ፥ በዱር በገደሉ የታገልነው ለመብትና እኩልነት ነው ማለታቸው ነው፡፡ ዛሬ የሀገራችን አጠቃላይ ይዞታና የሕዝቡን የኑሮ አባዜ ለተመለከተ፥ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎችን የትግል አላማ እየፈጸሙ ካሉት ውድመት ጋር አገናዝቦ ሊረዳው ይችላል፡፡ ሃቁ የሚያረጋግጥልን፥ ጠላትኢትዮጵያን ከፋፍሎ ለማዳከም የተጠቀመበትን የወረራ ዘመን መመሪያ ገልብጠው፥ ኢትዮጵያውያንን "በዘር" እና "በቋንቋ" ከፋፍለው እያጋጩ በደም አላባ የገዙበት፥ ሀገሪቱን በውዴታቸውና ለተግባራዊነቱም በብርቱ ታግለው የባህር በር አልባ ያደረጉበት፥ ሺዎችን ያጎሩበትና እልፍ አእላፋትን ያመሰቃቀሉበት አሰቃቂ ሁኔታ መንገሱን ነው፡፡ ለዚህ በዓይን ለሚታይ

ክሳራ ውጤት ደስተኞች ከሆኑ፥ በእርግጥም የህወሓት/ወያኔ መሪዎች የትግል ዓላማ፥ የሕዝብ መብትና እኩልነት ለማስከበር እንዳልነበር ለመተንተን መፈላሰፍ አያስፈልግም።

በሀገሪቱና ሕዝቧ ላይ እየተካሄደ ያለው አስከፊ የጥፋት ሂደት እንዲገታ፥ በብዙዎች ዘንድ በተደጋጋሚ ሰላማዊ መፍትሄ ቢሻትም፥ ለባለሥልጣኑ ሃይልና አቅፈው ደግፈው ለያዙት ሃይሎች፥ የሚጣጣምና የሚዋጥ ሆኖ አላገኙትም። ለገዥዎቹ እድሜ ማራዘሚያና ለደጋፊዎቹ ጥቅም ማስከበሪያ ሲባል፥ ሰላማዊ መፍትሄ በኢትዮጵያ ምድር እንዲመጣ በፍጹም የሚፈልጉ አልሆኑም። የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ብሄራዊ የምርጫ ውጤት ቁልጭ ባለ መልእክቱ የሚያስረዳንም፥ በሥልጣን ላይ ያለው ሃይል ከየት ወደየት እየመራንና እየተጓዘን መሆኑን ነው። አሁን በደረስንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሰላማዊውን መፍትሄ በር እንዲከፍት የሚገደደው ራሱ ወያኔ/ኢህአዴግ እንጅ፥ በዚህ ረገድ በሚደረገው ርብርቦሽ ሕዝብና ተቃዋሚዎች ተስፋ ከቆረጡበት ደረጃ ላይ በመሆናቸው፥ የተለየ የትግል ስልት እንዲከተሉ ከሚገደዱበት አጣብቂኝ ሁኔታ ላይ የደረሱ ይመስላል።

ወቅቱ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ተደጋግፎ የሄደ ወደ ብርሃን ይሻገራል፤ በቀቢጸ ተስፋ ዛሬም እንደትላንቱ ብቻዬን ሩጬ የዚያችን ማዶ የብርሃን ወለላ እልሳለሁ የሚል ካለም፥ ማራቸውን በሚከላከሉ ድንጉል ንቦች ገና መንገድ ላይ ተነድፎ ያልቃል። ከሁሉም በላይ ደግሞ፥ የሚታገሉትን ሃይል ተመክሮና ሥነ-ልቦና የማያውቁ የሕዝብ ወገኖች፥ ከራሳቸው ውድቀት ባሻገር ሕዝባዊውን ትግል በአያሌው ይጎዱታልና እንዲያስቡበት ይመከራሉ። ጉዞው ነገ ላይ ተቁሞ ብሄራዊ እርቅ ወርዶ የሕዝብን ሥልጣን ለማረጋገጥ ነውና፥ የሽሚያ ሩጫውና እርስ በርስ መጠላለፉ ያን ዓላማ እንደሚቃረን መገንዘብ ብልህነት ነው። ባለፉት ሥርዓቶች ጦስ የተቆሳሰሉ ቢኖሩ፥ ማምከኛው ሀገርን አድኖ ብሄራዊ እርቅ ነውና፥ ወደዚያው ተጉዞ ለመድረስና ለሀገራችን ደህንነት ሲባል፥ ጨለማውን በጋራ ማለፍ ያስፈልጋል። ዛሬ ሌላ ምርጫ የለም፤ የእርስ በርሱን መጎሻሸም ትቶ፥ እንዳባቶቻችን ክንድን አስተባብሮ ኢትዮጵያን ማዳን ብቻ ነው - ሌላው ሁሉ ቅራቅንቦ ምክንያትና አዘናጊ ጥያቄ ነው።